# የልጅ ድጋፍ በዲሲ፡ ጉዳይን መጀመር

የ ልጅ ድጋፍ ጉዳይ መጀመር የ ሚችሉባቸውአራት የ ተለያዩ መን ገ ዶች አሉ።

**1. የ ዲ.ሲን የ ልጅ ድጋፍ አገ ልግሎቶች ክፍል አዲስ ለ ማመልከት ይጠይቁ።**

የ ልጅ ድጋፍ አገ ልግሎቶች ክፍል ጉዳይ (The Child Support Services Division (CSSD)) ማለ ት በ ዲ.ሲ የ አባትነ ት እና የ ልጆች ድጋፍ ትዕዛዞችን የ መመስረት እና የ ማስፈጸም ስራ የ ሚሰሩ ጠበቆች ያሉት ኤጀንሲ ነ ው። ለ ችግረኛ ቤተሰቦች ግዜያዊ ድጋፍ (Temporary Assistance for Needy Families) (TANF) ወይም ሜዲኬይድ የ ሚቀበሉ ከሆነ ፤ CSSD የ ነ ጻ አገ ልግሎት ይሰጣል። በ TANF ወይም ሜዲኬይድ ውስ ጥ ካልሆኑ፤ የ ልጅ ድጋፍ አገ ልግሎቶች ክፍል የ 5$ ክፍያ (የ ገ ንዘብ ትዕዛዝ ወይም ቼክ ብቻ ለ ዲ.ሲ ገ ንዘብ ያዥ እንዲከፍሉ ይጠበቅቦታል)። ለ ተወሰኑ አገ ልግሎቶች ተጨማሪ ክፍያዎች ሊጠየቁ ወይም ከተሰበሰበ ማንኛውም የ ልጅ ማሳደጊያ የ ድጎማ ገ ንዘብ ላይ ሊቀነ ስ ይችላል። እባክዎን CSSD የ አባትነ ት እና የ ልጆች ድጋፍ ጉዳዮች ላይ የ ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ፍላጎቶችን የ ሚወክል መሆኑን አይዘንጉ። CSSD ግለሰብ ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን አይወክልም።

**እንዴት ማመልከት እችላለሁ?**

በ 202-442-9900 በ መደወል ቀጠሮ ማስያዝ ወይም ማመልከቻ መጠየቅ ይችላሉ። ወይም በ ድረ ገ ፅ http://www.cssd.dc.gov በ መግባት ማመልከቻውን ያውርዱ። ማመልከቻውን ሞልተውበ ማጠናቀቅ ይፈርሙ። የ ሚከተሉትን መረጃዎች የ ያዙ ኮፒዎችን (ኦሪጅናል ያልሆኑ) አያይዘውያቅርቡ፡

- የ እያንዳንዱን ልጅ የ ልደት ምስክር ወረቀት
- ማንኛውም አይነ ት የ መለያየ ት ስምምነ ት፣ የ ፍቺ ወረቀት፣ የ አሳዳጊነ ት ሙብት ትዕዛዝ ወይም የ አባትነ ት ማረጋገ ጫወረቀት፤
- ማንኛውም አይነ ት በ እጅ ያለ የ ልጅ ማሳደጊያ ድጎማ ትዕዛዝ (እ ወቅና ያለ ው)፤
- የ ገ ቢ መጠን ማረጋገ ጫ፤
- የ ዲ.ሲ የ ነ ዋሪነ ት ማረጋገ ጫ፤
- መታወቂያ (በ መንግስት የ ታተመ ፎቶ ያለ ውመታወቂያ)

**የ ማመልከቻውን እሽግ በ ፖስታ ይላኩ ወይም በ አካል ይውሰዱት ወደ:**

የ ልጅ ድጋፍ አገ ልግሎቶች ክፍል

ዋና ጠበቃ ቢሮ
441 4th Street NW, Suite 550 North
ዋሺንግተን ዲሲ 20001

**CSSD ሌላ እንዴት ሊረዳኝ ይችላል?**

ተጨማሪ መረጃ ለ ማግኘት ቢሮ መደወል ወይም በ አካል መጎ ብኘት ይችላሉ። የ ስራ ሰዓት ከሰኞ እስከ አርብ ከጥዋቱ 8፡ 15 እስከ ከሰዓት በ ኋላ 4፡ 45 ድረስ ነ ው።

**2. ለነ ፃ ጠበቃ ያመልክቱ**

በዲሲ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የሕጻናት ድጋፍ ጉዳዮች ላይ ሰዎችን የሚያግዙ በርካታ ነጻ የሕግ ድጋፍ አድራጊ ድርጅቶች አሉ። የልጆች ድጋፍ ጉዳዮችን የሚቆጣጠሩት ፕሮግራሞች ላይ ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት www.lawhelp.org/dc ወይም የቤተሰብ ፍርድ ቤት ራስ-አገዝ ማእከልን ይመልከቱ (የዚህን ገፅ መጨረሻ ይመልከቱ)።

## 3. የራስዎ ጠበቃ ይሁኑ

የልጅ ድጋፍ ጉዳይን ለመጀመር ጠበቃ አያስፈልጎትም። የሚፈልጉትን ህጋዊ ወረቀቶች (ትግባሬዎች) ማግኘት ይችላሉ በ www.dcbar.org/for-the-public/legal-resources/pro-se-pleadings.cfm, ወይም በዲ.ሲ ከፍተኛ ፍርድ ቤት፤ የቤተሰብ ፍርድ ቤት ማእከላዊ መቀበያ ማዕከል (500 Indiana Avenue NW, ክፍል JM-540)፤ ከሰኞ እስከ ዓርብ ከጥዋቱ 8:30 እስከ ከሰዓት በኋላ 5:00 ድረስ ክፍት ነው። ለበለጠ መረጃ "የልጅ ድጋፍ በዲሲ" በሚል የልጅ ድጋፍ ድጎማ ውሳኔ እንዴት እንደሚሰጥ የሚገልፀውን የመረጃ ገፅ ይመልከቱ።

### በመጀመሪያ አቤቱታውን ፋይል ያድርጉ

የአባትነት እና /ወይም የድጋፍ ማቋቋሚያ ማመልከቻን ይሙሉ። ወረቀቶችዎን ይውሰዱ ወደ ዲ.ሲ. ከፍተኛ ፍርድ ቤት፤ የቤተሰብ ፍርድ ቤት ማእከላዊ መቀበያ ማዕከል። የማመልከቻ ክፍያ 80$( (ዋና ዋና ክሬዲት ካርዶች፣ ጥሬ ገንዘብ ወይም የገንዘብ ማዘዣ በመጠቀም) መክፈል ይጠበቅቦታል። ክፍያውን ለመክፈል አቅም ከሌሎት ፍርድ ቤት የፍርድ ቤት ክፍያዎች እና ወጪዎች ሳይከፍሉ እንዴት ማመልከት እንደሚችሉ የሚገልጽ ማብራሪያ የያዘውን "የነፃ የአገልግሎት ክፍያዎች በዲ.ሲ" በሚለው ውስጥ ያለውን የመረጃ ወረቀት ያንብቡ። የጉዳይዎን ፋይል በሚያደርጉበት በዚያኑ ቀን ጉዳዮን ለመስማት በ45 ቀናት ውስጥ የችሎት ቀጠሮ ይሰጥዎታል። የቅድመችሎት ቀንዎን የሚያሳዩ ማሳወቂያውን (Notice of Hearing and Order Ordering Appearance (NOHODA)) የማእከላዊ መቀበያ ማዕከል ያቀርብልዎታል።

### በመቀጠል አቤቱታዎን ያቅርቡ።

የአቤቱታው ማመልከቻ ቅጂ እና የቅድመችሎት ቀኑን የሚያሳየውን ማሳወቂያ ሌላኛው ወላጅ እንዲደርሰው ማድረግ አለብዎ። ይህንን ማድረግ የሚችሉበት ሌሎች አራት መንገዶች አሉ፡

1. በግል አገልግሎት ሰጪአማካይነት፡ ማመልከቻውን እና የቅድመችሎት ቀኑን የሚያሳየውን ማሳወቂያ በቀጥታ ለማድረስ በጉዳዩ ላይ ምንም ተሳትፎ የሌለው አዋቂ ሰው ይጠይቁ። ይህንን እርሶ ራስዎ ማድረግ አይችሉም። ወረቀቶቹን ለማድረስ ጓደኛ፣ ዘመድ፣ ወይም መያዊ የስራ ሂደት አገልጋዮችን መጠየቅ ይችላሉ።
2. በቤት ውስጥ የምትክ አገልግሎት፡ በጉዳዩ ውስጥ ያልገባ አንድ አዋቂ ሰው የሌላኛው ወላጅ ቤት ሄደው ማመልከቻውን እና የቅድመችሎት ቀኑን የሚያሳየውን ማሳወቂያ በቀጥታ እዚያ ለሚኖር አዋቂ የሆነ ሰው እንዲሰጥ ይጠይቁ። ይህንን እርሶ ራስዎ ማድረግ አይችሉም። ወረቀቶቹን ለማድረስ ጓደኛ፣ ዘመድ፣ ወይም መያዊ የስራ ሂደት አገልጋዮችን መጠየቅ ይችላሉ።
3. ተለዋጭ አገልግሎት በስራ ቦታ፡ በጉዳዩ ውስጥ ያልገባ አንድ አዋቂ ሰው የሌላኛው ወላጅ የስራ ቦታ ሄደው ማመልከቻውን እና የቅድመችሎት ቀኑን የሚያሳየውን ማሳወቂያ በቀጥታ እዚያ ለሚሰራ አዋቂ የሆነ ሰው እንዲሰጥ ይጠይቁ። ይህንን እርሶ ራስዎ ማድረግ አይችሉም። ወረቀቶቹን ለማድረስ ጓደኛ፣ ዘመድ፣ ወይም መያዊ የስራ ሂደት አገልጋዮችን መጠየቅ ይችላሉ።

4. እወቅና ያለው ደብዳቤ እና የአንደኛ ደረጃ ደብዳቤ: ማመልከቻውን እና የቅድመ ችሎት ቀኑን የሚያሳየውን ማሳወቂያ ለሌኛው ወላጅ ተመላሽ ደረሰኝ በሚጠይቀው እወቅና ባለው ፖስታ ይላኩ። ይህንን ፖስታ ቤት በመሄድ ራስዎ ማድረግ ይችላሉ። ደብዳቤው ከተላከ በኋላ ፖስታ ቤቱ ተመላሹን ደረሰኝ ("አረንጓዴ ካርድ") ወደ እርስዎ ይልካል። የአቤቱታው ማመልከቻ ቅጂ እና የቅድመ ችሎት ቀኑን የሚያሳየውን ማሳወቂያ እውቅና ባለው ፖስታ በላኩበት በተመሳሳይ ቀን ማመልከቻውን እና የቅድመ ችሎት ቀኑን የሚያሳየውን ማሳወቂያ ሁለተኛ ቅጂ በአንደኛ ደረጃ ደብዳቤ ለሌላኛው ወላጅ ይላኩ። ፍርድ ቤቱ (1) ሌላኛው ወላጅ አገልግሎቱ ላይ ከተደነገገው የመልሶ መጠየቂያ ደረሰኝ ላይ ከፈረመ ወይም (2) ሌላ በሚኖርበት ቤት ውስጥ የሚኖር ወይም በሚሰራበት ቦታ የሚሰራ አዋቂ ሰው ደረሰኙ ላይ ፈርሞ ከመለሰ አገልግሎቱን እንደ "መልካም" ይወስደዋል። ማንም ተመለሽ ደረሰኙ ላይ ካልፈረመ ነገር ግን በአንደኛ ደረጃ ደብዳቤ የተላከው ቅጂ ካልተመለሰ፤ አገልግሎቱ የልጅ ድጋፍን በተመለከተ "ጥሩ" ይቆጠራል ነገር ግን በአባላትነት ጉዳይን አያካትትም።

**ከዚያም የአገልግሎቱን የምስክርነት ቃል ፋይል ያድርጉ።**

የአገልግሎቱ የምስክርነት ቃል ሌላኛው ወላጅ እንዴት ማመልከቻው እና መልእክቱ እንደደረሰው በመግለፅ የሚያረጋግጥ የመሀላ ቃል ነው። የርስዎን የምስክርነት ቃል በቤተሰብ ፍርድ ቤት ማእከላዊ መቀበያ ማዕከል ውስጥ ማስገባት ይኖርብዎታል። ሌላው ወላጅ በግል ወይም በምትክ አገልግሎት ማመልከቻው የደረሰው ከሆነ ፤ መልዕክቱን ያደረሰው አዋቂ ሰው ምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተው ማጠናቀቅ አለባቸው። ሌላኛው ወላጅ ማመልከቻው የደረሰው እውቅና ባለው ደብዳቤ እና በአንደኛ ደረጃ ደብዳቤ ከሆነ ፤ እርሶ የምስክርነት ቃሎን ሰጥተው ማጠናቀቅ ይኖርቦታል።

**ችሎት ላይ መገኘት።**

የገቢ መጠንዎን ማረጋገጫ፣ የህፃኑ የጤና መድን ወጪ፣ የልጆች እንክብካቤ ወጭዎች፣ ተጨማሪ የልጁ ወጪዎች፣ እና ስለሌላኛው ወላጅ ያሎትን ማንኛውም አይነት መረጃዎች ይዘው ይገኙ።

**4. የግል ጠበቃ የይቅጠሩ**

የልጆች ድጋፍ ጉዳዮችን የሚይዙ የግል የህግ ባለሙያዎችን ዝርዝር ለማግኘት የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የሕግ ባለሙያ የማጣቀሻ አገልግሎት ባር ዳሬቲን ላይ የመስመር ላይ የዳሰሳ ጥናት https://badc.barlrs.com ላይ ሙሉ ። የጥቆማ አገልግሎቱ 39.95 $ ያስከፍላል። እንዲሁም ከቤተሰብ እና ከጓደኞች ማጣቀሻ ማግኘት ወይም መስመር ላይ መፈለግ ይችላሉ።